# በጀርመን የገባውን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን በተመለከተ ያለው ቴክኒካዊና ተቋማዊ ልምድና አስተያየት - ክፍል 2

**ለተከበራቹህ ወገኖች** **16.03.2020**

ከ15 ቀን በፊት የኮሮና ቫይረስን በተመለከት ከጀርመን ያለውን ቴክኒካዊ ልምድና አስተያየት ስፅፍ ኮሮና ጀርመን ከመግባቱ እና ኢትዮጵያም ከመገኘቱ በፊት ነበር። አሁን ደግሞ ወረርሽኙ ገብቶ በጥቂት ቀናት ውስጥ አፈሻል በተሰጠው መርጃ ወደ 7000 ሰው ከያዘ እና የ13 ሰዎች ህይወትን ከቀጠፈ በኋላ ያለውን ሁኔታ እና በሰዓታት ውስጥ በሚከሰቱ ኑሮዋችንን በተመለከት እየተደርጉ ያሉ የተለያዩ ፈጣን ገደቦች እና ለውጦችን ልምድ ለማካፈል እሞክራለሁ።

ወረርሽኙ እንደሚታወቀው በአብዛኛው ለከፍተኛ የጤንነት አደጋ የሚዳርገው የበሽታ መከላከል አቅም ያነሳቸውን፣ እድሜያቸው የገፋውን፣ አገጋሚዎችን እና ከባድ ህመም ያለባቸውን ነው። ለምሳሌ በአንድ ቀን ውስጥ ብቻ በወረርሽኙ የሞቱትን 4 ሰዎች ከተመለከትን እድሜያቸው ከ80 አመት በላይ ናቸው። ከዚህ በፊት የሳንባ በሽታ ተጠቂ (የሳንባ ነቀርሳ፣ አስማ፣ ወዘተ) የሆኑትን ሰዎች እድሜም ሳይለይ የሚይዝ ነው።

## ጀርመን ውስጥ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል ?

ቫይረሱ „በመባዛት እድገት“ (exponential growth) እየተስፋፋ ቢሆንም ከፍተኛ የመረበሽ እና የመደናገጥ ስሜት ባጠቃላዩ አይታይም። ግን የተወሰኑ ሸቀጦች እና መድሃኒቶች በተለይም የእጅ ማፅጃ አልኮሆል እና የህመም ማስታገሻ እጥረት አለ፡፡ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ስለሌለ ይህንን አድርገን አንቀሳቀስም። ካለም ሊጠቅም ወይም ቅድሚያው መሰጠት ያለበት ለታካሚዎች፣ ለተጠረጠሩ፣ እነሱን ለሚያክሙ እና ለበጎ አድራጎት አገልጋዮች ነው። ይህም ትክክል አሰራር ነው። „እጥረት ፈጣሪ ያደርጋል“ እንዲሉ ጣሊያን በስስ ሻሻቸው አፍና አፍንጫቸውን በመሸፈን ሲጠቀሙ ታይተዋል። መጀመሪያ ጀርመን ሲገባ ሰው በመጠራጠር ለማወቅ ወደ የኮርና መመርመሪያ ማእከል በመሄዱ ቁጥሩ ከፍተኛ ሰው እስከ 7 ሰዓት ወርፋ ይወስድበት ነበር፡፡ አስቀድሞ አንዳንድ ደረቅ የሆኑ ነገሮችን ገዝቶ ማስቀመጥ ቢጠቅምም በብዙ ሱፐር ማርኬቶች መስርታዊ ፍጆታዎችን ገዝተው በሚያከማቹ ሰዎች ተሙዋጦ መታየቱን ተገንዝቤያለሁ።

## በበርሊን ከተማ እና በጀርመን ግዛቶች

- የከተማው የኮሮና መከላከያ ደንብ በከተማው ምክር ቤት ጸድቆ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል።
- ሁሉም ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ተዘግተዋል፡፡
- አብዛኛው አውቶቡሶች ከባቡር በስተቀር ሲያቆሙ፣ የባቡር እንቅስቃሴም ቀንሷል።
- ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች ተሰርዘዋል።
- ባሮች፣ ክለቦች፣ ልዩ የደስታ መዝናኛ ቤቶች ተዘግተዋል።
- ቡና ቤቶች ፣ ቲያትሮች፣ ሲኒማ ቤቶች ተዘግተዋል።
- በየቤቱ እየተዞሩ የሚደርጉ ጥናቶች፣ ምርመራዎች፣ ቃለ መጠይቆች ቆመዋል።
- 9 የበርሊን ፖሊሶች በስራ ላይ በወረርሽኙ በመያዛችው ወደ 300 የሚሆኑ የቅርብ ባልደረቦቻቸው ወደ ልዩ ማቆያ ቦታ ገብተዋል።
- ሆስፒታሎች ቀዶ ጥገና የታሰበላችውን ግን እጅግ አስቸኳይ ያልሁኑትን ቀጠሮዎች በማራዘም አልጋዎች ለኮሮና ታማሚዎች ለማዘጋጀት እየሰሩ ነው።
- የሃይማኖት ተቋማት የፀሎት አገልግሎት በቤት ውስጥ እንዲያደርጉ ምክር እየሰጡ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በጀርመን እና አካባቢው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሓዶ ቤተ ከርስቲአያን ምእመናንን ፀሎታቸውን ከቤት እንዲያደርጉት አሳስቧል።

- እቃ አድራሾች (delivery service) ክፍያውን በኢንተርኔት (online) ወይም በካርድ እንዲሆን ሲመክሩ ወደ ቤት የሚያደርሱትም በር ላይ አስቀምጠው መሄድም ጀምረዋል።



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

- ሬስቶራንቶች የሚፈቀድላቸው ጠረጴዛዎቻቸው 1.5 ሜትር ማራራቅ ሲችሉ ነው። የእንግዶቻቸውን ስምም እንዲመዘግቡ ይጠየቃል። ከረቡዕ ጀምሮ እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት (6:00 p.m.) ድረስ ክፍት ይሆናሉ። ይህ መመሪያም ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ አይታወቅም።
- የህፃናት ማሳደጊያ፣ በእድሜ የገፉ ሰዎች ማቆያ እና የአካል ጉዳተኞች ማዕከል ከጥቂት ልዩ ምክንያቶች ካለው በስተቀር ከውጭ ሌላ ሰው አይገባም፣ አይጎበኝም።
- ህፃናትና ወጣቶችን አያቶቻቸውን እንዳይጎበኙ በጥብቅ ይመከራል።
- አመቺ ሁኔታ የፈቀደለንም ከቤት ቢሮ (Home Office) መስራት ጀምረናል ፡፡
  - (የቤት ቢሮ ማለት የሥራ እና የግል ኑሮ-ሚዛን በመሆን መጫናነትን ለማስወገድ እና ጊዜን ለመቆጠብ የሚረዳ ሲሆን በተለይም ተላላፊ በሽታዎች ሲገኙ በውጤታም መልኩ ስራን ሳያቋርጡ ለመስራት ያስችላል። ወስኙ ቢሮ የሚሰራ በኮምፒተር ወይም የፅሁፍ ስራ፣ የቴሌፎን ስራ፣ ወዘተ ሲሆን ኮምፒተር/ላፕቶፕ፣ ተደራሽ የሚያደርግ ኢንተርኔት እና ስልክ/ሞባይል ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው።)
- የተማሪዎች ቤት መዋል ለቤት ቢሮ የማያምች የስራ ባህሪይ (ለምሳሌ አስተዳድራዊ ያልሆነ የምርት ስራ እና ግልጋሎት) ያላቸው ወላጆች ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ይታሰባል።
- ጀርመን ውስጥ ያሉ የአውሮፕላን ጣቢያዎችን እና ሱቆች (ሱፐር ማርኬትን ሳይጨምር) ለተወሰነ ጊዜ ለመዝጋት እቅድ ተጀምሯል። ከመጪው ረቡዕ ጀምሮ ወደ ጀርመን መግባትና መውጣት ለተውሰነ ጊዜ ይታገዳል።
- ከመጪው ረቡዕ ጀምሮ ለመሰርታዊ ፍጆታ ከሚያስፈልጉ ሱቆች በስተቀር የተለያዩ የገብያ መደብሮች፣ ቤተ ክርስትያናት፣ መስጊዶች፣ ምኩራቡች፣ ወዘተ ይዘጋሉ።
- በወረርሽኝ የተነሳ አብዛኛው የፓርላማ አባል ባይገኝ ህግን እንዴት መወሰን የሚያስችል አንቀፅ ለማውጣት እና የህገ መንግስት ማሻሻያ ለማድርግ የጀርመን ፓርላማ ቀጠሮ ይዟል።

## የስፖርት እንቅሰቅሴዎች

በአካባቢያችን ከሚገኘው ሃይቅ ለመሮጥ ስሄድ ሰው ረጋ ብሎ ንፁህ አየር ለመናፈስ ማየቴ እና ስፖርቱን በነፋሻ ቦታ መስራቱን ተመልክቼያለሁ። ይህም የሚያበረታታ ነው። በርሊን ማንኛውም አይነት የስፖርት ጅም ቢታገድም ሰው የሰውነት እንቅስቃሴውን እና ውጭ ሂዶ መስራቱን አልገደበውም። ጤና ተኮር ስፖርት የበሽታ መከላከያ አቅምን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። ቢሆንም

- የጀርመን ቡንደስሊግ ጨዋታ እንደተቋረጠ ይቆያል።
- የስፖርት ዝግጅቶች እንደ በርሊን "ግማሽ" ማራቶን ተሰርዘዋል።
- ጂምናስቲክ እና የስፖርት ማዕከሎች ተዘግተዋል፡፡
- የሻምፒዮን ሊጋ UEFA ወደ ሰኔ እና ሐምሌ ሊተላልፍ ሲታቀድ።
- የአውሮፓ የእግር ኳስ ሻምፒዮናም ሊተላልፍ ይችላል።
- ውድድር ተኩር የሆነው የእግር ኳስ ተጫዋቾችነት ለቤት-ቢሮ ባይሆንም የጀርመን ቡንድስ ሊግ ተጫዋቾች የተናጠል ልምምድ ፕሮግራም ተሰጥቶችው ከቤታችው ልምምድ ያደርጋሉ።
- የበጋ ኦሎምፖክ እንደማይሰረዝ የአለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሜቴ ቢገልፅም ለኦሎምፒክ ማጣሪያ የሚያደርጉ አብዛኛዎቹ የስፓርት አይነቶች ማጣርያዎቻቸውን በማራዘማቸው የጊዜ ሰሌዳው ላይ ችግር መፍጠሩ አይቀርም።

## ኮሮና እና አውሮፓ

- የጀርመን የጤና ሚኒስተር በጡረታ የተገለሉ የህክምና ባለሙያዎች ጥሪ አደርጎላቸዋል።
- የጀርመን መከላከያ ሰራዊት ተጠባባቂዎችን በበጎ አድራጎት እንዲሰማሩ ጥሪ አድርጎላቸዋል።
- ከአውሮፓ ህብረት አገራት ውጭ የሆኑ ዜጋዎች ከልዩ ምክንያት በስተቀር እንዳይገቡ የሚከለክል መመሪያ በቅርብ ይወጣል።
- ስፔን የአስቸኩዋይ ጊዜ አዋጅ በማውጣት ሰዎች ልዩ ፈቃድ ያላችው ካልሆኑ በስተቀር ቤታችውን መልቀቅ አይችሉም።



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

- ስፔን ከፍተኛ ፖሊስ በማዝመት፣ ድምፅ ማጉያ በተጠመደላቸው ድሮኖች ከአየር ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን የተመለከተ እና ህብረተሰቡ ምን ማድረግ እንደሚገባው እየገለፁ እና እየተቆጣጣሩ ይገኚል።
- ስፔን ብዙ ሆቴሎች ክፍላቸውን በነፃ ለታማምዊች እንዲሆን አቅርበዋል።
- ስዊዘርላንድ አንድ ወር የሚቆይ የአስቸኩዋይ ጊዜ አዋጅ በሚቀጥሉት ቀናት ያውጃል።
- አስትሪያ ማንኛውም አይነት ስብሰባዎች ስትዘርስ፣ ከ5 ስዎች በላይ አብርው እንዳይገኙም ተከልክሏል።
- ቤልጅግ በውጭ ያሉትን ዜጎችዋን በሙሉ ወደ አገር እንዲገቡ ጠርታልች። እነሱም ለ14 ቀን ልዩ ማቆያ ቦታ ይገባሉ።
- በአለማቀፍ የፓስፖርት አመዳደብ ደርጃ በሁለተኛ ደርጃ የሚገኘው እና 128 አገሮችን ያለቪዛ ማስጎብኘት የሚያስችለው የጀርመን ፓስፖርት የያዘ እና መነሻውን ጀርመን ያደረገ እንኳን አሜሪካ እና ጎርቤት አውሮፓ አገሮችን ቀርቶ አፍሪካ ውስጥ እንደ ዩጋንዳ እና ናሚቢያ ለመግባት አይችልም።
- ፈረንሳይ ከፋርማሲ፣ ባንክ እና ሱፐር ማርኬት በስተቀር ሌላው ዝግ  ነው።
- ጣሊያን ውስጥ የአስቸኳይ አዋጁ ከተደነገገ በኋላ ከ20ሺ በላይ የደንብ ጥሰት በአንድ ሳምንት ውስጥ ተመዝግቧል።

## ኢኮኖሚያዊ ክስረት

በአጠቃልይ በኮሮና የተንሳ በብዙ መቶ ቢሊዮን ዩሮ እስከ ትሪሊዮን ሊደርስ የሚችል ክስረት በአለም የኢኮኖሚ ይዘት ላይ ይጠበቃል። ለምሳሌ

- የአለም የአየር ትራንስፖርት እስከ 113 ቢሊዮን ዶላር እንደሚከስር ሲገመት።
- ሉፍታንዛ ብቻ ወደ 23 ሺ የሚቆጠሩ በረራዎችን በአንድ ወር ብቻ ሰርዟል።
- በቀን 1300 በረራዎችን  የሚያስተናግደው የፍራንክፈርት አውሮፕላን ማረፊያ 40 ከመቶ የሚሆኑ ተሳፋሪዎች ቀንሷል። በአሁኑ ወቅት በየቀኑ ወደ 70,000 የሚሆኑ ተሳፋሪዎች በየቀኑ እየቀነሰ ነው።
- አፕልም በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙትን ሱቆቹን ለተወሰነ ጊዜ መዝጋት ጀምሯል።
- በሚልዮን የሚቆጠሩ የሆቴሎች ምዝገባዎች መሰርዛቸው ከፍተኛ ኪሳራን ፈጥሯል። (የአለም የቱሪዝም አቅም እስከ 6,7 ትሪሊዮን ዶላር ይደርሳል።)
- የስፖርት ትጥቅ አምራቹ የአዲዳስ ኩባንያ ብቻ ወደ አንድ ቢሊየን ዮሮ እንደሚያጣ ይገምታል።
- የጀርመን እግር ኳስ ወደ 700 ሚሊዩን ዮሮ ክስረት ይጠበቃል።
- በሌላ በኩል ቤንዚን እና ናፍጣ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መወርድ ተጠቃሚውን ሲያስደስት በነዳጅ አምራች አገሮች ላይ ኪሳራ አምጥቶባቸዋል።
- መንግስት በሚወስደው እርምጃ የሚደርሰውን ክስረቶችን ለመደጎም በጀት ለመመደብ እየታሰብ ሲሆን፣ ቋሚ ስራ የሌለውን፣ በባንክ፣ በኢሽንት፣ በመኪና አምራች፣ በቱሪዝም እና ሆቴል፣ ሪስቶራንት፣ ትያትር፣ ፊልም ኢንዱስትሪ እና ስፖርት ሴክተር ላይ በአብዛኛው ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ይደርስባቸዋል።

## ማጠቃለያ

„በሽተኛ የሆነ ሀብታም ሰው ግማሽ ደሀ ነው።“ እንደሚባልው ጤንነት ከገንዘብ ይበልጣል።

የዚህ ሁሉ አላማ የበሽታው መስፋፋትን መድሃኒት / ክትባት እስኪገኝለት ድረስ ለማዝገም ነው። ሁሉም በመተባበር እና የሚሰጠውን መመሪያ የሚከትል ከሆን፣ አስቀድሞ መከላከያዎች ላይ ትኩረት ከተሰጠ እና ከሚሰራጩ የሐሰት የሶሻል ሜዲያ ዜናዎች ከራቀ መልካም ውጤት ይገኛል።

በህክምና ምርምር እና ቴክኖሉጂ ልቀት በአለም ላይ ቀዳሚውን ድርሻ የያዙ ጀርመኖች የቫይረስ መመርመሪያውን እንደፈጠሩ ሁሉ በከፍተኛ ፍጥነት ክትባት ላይ እየሰሩ ነው። የጀርመንን ሮበርት ኮህ አንስቲትዩት ከፍተኛውን ድርሻ በኮሮና መከላከል ላይ የያዘ ነው። ሮበርት ኮህ 1882 የሳንባ ነቀርሳ መድሃኒትን ያገኘው ነው።  የአሜሪካ መንግስት የኮሮና ቫይረስ ክትባትን ለማግኘት የተቃረበውን የጀርመን ባዮቴክ ኩባንያ CureVac በከፍተኛ ገንዘብ ለመግዛት ያቀረበውን ጥያቄ ጀርመን ለአንድ አገር ብቻ የሚሆን ሳይሆን በመተባበር የሚሆን ነው በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል።



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

ለቫይረሱ መስፋፋት ቀዝቃዛ የአየር እርጥበት ወይም የአየር ማቀዥቀዣ በብዛት የሌለብት እና በሽታ የመቋቋም ችሎታ ያላቸው ወጣቶች የበዙበት አፍሪካ በበሽታው እስካሁን በፍጥነት ባይጠቃም በሽታው እዚያም ሊስፋፍ እንደሚችል ይታሰባል፣ ገብቷልም። ስለዚህም የአፍሪካ አገሮች በተለይም ኢትዮጵያ ከዚህ ብዙ መማር፣ የአደጋ መከላከያ እና አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ስረኣት (early warning system) ማዘጋጀት ይገባል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሞራል ውጭ የሆኑ የተጋነኑ ዋጋዎችን ለመከላከያ/ የአፍ እና የአፍንጫ ጭንብል የሚጠይቁ ጨካኝ ነጋዴዎችን መቆጣጠር መጀመሩን የሚያመሰገን ጥሩ ሥራ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ደህንነት እና ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲፋጠር ከዚህም ያለፍ ውሳኔ መውሰድ ግድ ነው። ከሳምንታት በፊት የፈረንሳይ ፕሬዝዳንት ማክሮን ሁሉንም የአፍ እና የአፍንጫ መከላከያ እና አልባሳት እንዲወረስ ትእዛዝ ሲሰጡ ጀርመን ደግሞ እነዚህን  ኢክስፖርት ማድረግ ከልክሏል።

በተጨናነቀ ግርግር ሰው ተረጋግጦ አደጋ የሚደርስበት ሁሉም ተደናገጦ በደመነፍስ የራሱን  ህይወት ብቻ  ለማትረፍ ሲሮጥ ነው።  በኮሮናም እንደዚሁ ነው። በመረጋጋት፣ በሰከነ እና የቅደም ተከተልን አካሄድ በጠበቀ መልኩ የጋራን ጤንነት ማስቀደሙ የራስንም ይጠብቃል። የሀሰት ዜናዎች ከማመን፣ በሽታውን መደበቅ እና ምስጢር ማድረግ የሌሎችን ህይወት በገዛ እጃችን አስገብተን መፍረድ ስለሚሆን ከዚህ ተግባር መራቅ የመጀመሪያ ተግባር ነው። ጉንፋን እንደማይደበቅ ሁሉ ኮሮና የያዘው ሰው መደብቅ የለበትም። ምልባትም ሳናውቀው ምልከቱን ሳይታይብን ይዞንም፣ ይዞኝም ሊሆን ይችላል። ዋናው ነጥብ ንክኪነትን ማስቀረት፣ የእጅ ንፅህና፣ ሰው የበዛበት ቦታ አለመገኘት (social distancing)፣ ያለመደናገጥ፣ የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርዓቶችን ማጠንከር እና የመቋቋም አቅምን ማጎልበት ላይ ነው። በተለይም ወጣቶች ኃላፊነት ወስደው በበጎ አድራጎት ተሳትፎ የመርዳት ታሪካዊ ግዴታ አለባቸው። ጀርመን የበጎ ፈቃደኛ ማህበሮች እና ቡድኖች አቅም የሌላቸውን ሰዎች ለመርዳት ሰዎችን በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። በተለይም ጎርቤቶች  „Nachbrschaft“ እና„nebenan.de“ በመባል የሚታውቁት የኢንተርኔት ፖርታሎች ቀዳሚ ናችው።

የአለም ጤና ድርጅት (World Health Organization) የጤና ባለሙያዎች እና የሚመለከታችው ባለስልጣናት የሚሉትን በተረጋጋ ሁኔታ መከተል እና መስማት ያስፈልጋል። ጀርመን ልዩ የማቆያ ቦታ ጥሰው በሚገኙት ላይ ከገንዘብ እስከ 2 አመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል።

በሽታውን የመቋቋም ችሎታ ያላቸው ህፃናት እና ወጣቶች ቤት እንዲውሉ መደረጉ በቅድሚያ እነሱን ይይዛቸዋል በሚል ፍራቻ ሳይሆን፣ ቫይረሱን ያለምንም ምልክት በመሸከም ወደ ወላጆቻቸው ሊያስተላልፉ ስለሚችሉ እና እነዚህም በብዛት እና ባንድ ጊዜ ለጥቂት ቀናትም እንኳ በቀላሉ ቢታመሙ፣ ከስራ ቢቀሩ አጠቃላይ ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ሊፈጠር ስለሚችል ነው።

አውሮፓ ውስጥ ከላይ የተጠቀሱት እርምጃዎች ከተጠበቁ ይህ „በመባዛታዊ እድገት“ የሚስፋፋው ወረርሽኝ እንደሚገታ እና ለዚህም ቢያንስ 8 ሳምንታት እንደሚፍጅ ይጠበቃል።

በኮሮና ወረርሽኝ ላይ እየተደረገ ያለው ርብረብ፣ እየተንቀሳቀስ ያለው ሃይል አዲስ የአስተሳሰብ ለውጥ እና ባህሎችን፣ የወደፊቱን ጤና መዋቅር ላይ ትኩረት የሚያመጣ ነው። ወረርሽኙ መተባበርን፣ መቀራረብን፣ አገሮችን፣ ደሃን እና ሃብታምን አንድ የሚያደርግ ሁኔታም ፈጥሯል።

የዚህ ፅሁፍ ይዘት በሰአታት በሚቀያየርው ሁኔታ እና በሚወስዱ እርምጃዎች የተንሳ ወቅታዊ ላይሆን ይችላል።

ከመልካም የጤና ምኞታዊ ሰላምታ ጋር

ፀጋዬ ደግነህ (ዶ/ር)

ዶ/ር ፀጋዬ ደግነህ ጉግሳ

በርሊን መጋቢት ፯ ፪፻፩፪ ዓ.ም. (*Berlin, 16 th March, 2020*)



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh